# የኢትዮጵያዊያን ትግል – ( የመጨረሻው - ክፍል አራት )

## ከዚህ ወዴት?

ሰኔ ፲፰ ቀን ፳ ፻ ፭ ዓመተ ምህረት - June 25, 2013

ከአንዱ ዓለም ተፈራ - የእስከመቼ አዘጋጅ፤ Facebook እና Twitter → eske.meche@yahoo.com
http://nigatu.wordpress.com/

ከሁሉ በፊት እያንዳንዳችን ለማመን የማንፈልገው፤ በልባችን ግን በደንብ የምናውቀውን ሀቅ ላስቀምጥ እፈልጋለሁ። በታጋይ ኢትዮጵያዊያን ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ፤ ጎደለም በዛም የራሳቸው የሆኑ ደጋፊዎች አሉዋቸው። እኒህ አባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው፤ ለኢትዮጵያዊያን ነፃነት ገደብ የሌለው መስዋዕትነት ለመክፈልና ሀገራቸው አድጋና በልፅጋ ለማየት የተነሱ ናቸው። ይኼን ሀቅ ካገናዘብን፤ ይህን ሁሉ ኃይል፤ በዚህ ጽሑፍ በክፍል አንድ፣ ሁለትና ሶስት በተደረደሩት ሃሳቦች ተመርኩዘን ወደ አንድ ማጠቃለል እንዴት ይቻላል? ከዚህስ ወደ የት እንሄዳለን? የሚለውን በዚህ የአራተኛውና የመጨረሻው ክፍል አስቀምጣለሁ። መከተል የግድ ያለብን ሶስት የጠሩ ቁም ነገሮች አሉ። አንደኛ የጠራ የትግል ዓላማ መኖሩ ነው። ይህ እንግዲህ በግልፅ የሠፈረ ራዕይ ተነድፎ፤ በተራ ቅደም ተከተል የተቀመጠ የትግል መመሪያ ነው። ሁለተኛው የጠራው ጉዳይ ደግሞ አንድ ድርጅት መመሥረቱ ነው። በቁጥር አንድ የተጠቀሰውን ራዕይ ተመርኩዞ፤ የተደረደሩትን ቅደም ተከተል የትግል ሂደቶች ለማካሄድ፤ ከሞላ ጎደል አብዛኛውን ኢትዮጵያዊያንን ወደ አንድ የማሰባሰቡና የማዋቀሩ ጉዳይ ነው። በሶስተኛ ደረጃ የቀረበው የጠራው ጉዳይ የአመራር ሰጪው ጉዳይ ነው። ይኼን በቁጥር አንድ የተጠቀሰ ራዕይና በቀጥር ሁለት የተዋቀረ ድርጅት፤ አንድ ትግል፣ አንድ ግብ፣ አንድ አጀንዳና አንድ ዓላማ አስይዞ፤ በአንድ ድርጅት ሥር አምጥቶ በብቃትና በጥራት የሚመራውን ክፍል ማበጀቱ ነው።

እስኪ በኢትዮጵያዊነታቸው አመኑም አላመኑም ታጋይ ኃይሎችን እንዘርዝራቸው። ይህ ዝርዝር ሁሉን የኢትዮጵያ ታጋይ ድርጅቶች የያዘ አይደለም። ሁሉም ደግሞ በኢትዮጵያዊነታቸው የጠራ አቋም አላቸው ማለት አይደለም። የማላውቃቸውና ሕልውናቸውን ያልሰማኋቸው ሌሎች ሊኖሩ እንደሚችሉ እገነዘባለሁ። ሆን ብዬ የዘለልኳችሁ ሳይሆን፤ ባለማወቅ ላልዘረዘረኳችሁ ይቅርታዬን አስቀድማለሁ።

### <u>በሀገር ውስጥ፤</u>

<u>ሰማያዊ ፓርቲ</u>፣ <u>የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት</u>፣ <u>በመድረክ ዙሪያ የተሰባሰቡት ድርጅቶች በሙሉ</u>፣ <u>በትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት ያልተኮለኮሉ ለህዝብ የቆሙ ታጋይ ድርጅቶች</u>

### <u>ከሀገር ውጪ፤</u>

<u>የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ</u>፣ <u>የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ)</u>፣ <u>በሕብረት ውስጥ የተጠቃለሉ የፖለቲካ ድርጅቶች</u>፣ <u>ግንቦት ሰባት</u>፣ <u>ግንቦት ሰባት (ዴሞክራሲያዊ)</u>፣ <u>የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር</u>፣ <u>የተለያዩ የአካባቢ ነፃ አውጪ ግንባሮች</u>

### <u>የኅብረተሰብ ማህበራት፤</u>

<u>በሸንጎ የተጠቀለሉ ብዙኀን ማህበራት</u>፣ <u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሽግግር ካውንስል</u>፣ <u>ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ</u> ናቸው።

እዚህ ላይ አንድ ነገር በጥብቅ ላሠምር እፈልጋለሁ። እነዚህ ድርጅቶች፤ በዕድገት ሂደታቸው ያሰባሰቧቸው የድርጅት አባሎቻቸው፤ በድርጅት ዙሪያ ካልተሰበሰቡት የበለጠ የሀገር ፍቅርና ለነፃነት የትግል ፍላጎት ያላቸው ናቸው። በውጭ በምንገኘው ኢትዮጵያዊያን መካከል እነዚህን በመዝለል ሌላ አባሎችን ፈልጎ ለትግል ለማሠለፍ የሚደረግ ጥረት፤ ሀቅ ይጎድለዋል። በእርግጥ በወጣትነት የእድሜ ክልል ያሉና በጠቅላላ የፖለቲካ ትርምስምሱ ተስፋ በማጣት ራቅ ያሉ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ለመኖራቸው ጥርጥር ሊኖረን አይገባም፤ ሆኖም ግን፤ በድርጅት ተጠቃለው የሚታገሉት የላቀ የሀገር ፍቅርና የወገን ተቆርቋሪነት አላቸው ብዬ አምናለሁ። ታዲያ ከላይ የተዘረዘሩት ድርጅቶች፤ የያዟቸውን አባሎች በሙሉ ባንድ ላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና አንድነት አሠልፈው፤ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥትን ለማስወገድ ከተነሱ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀድሟቸው ከፊት ይሠለፋል። እንዴት ባንድ ላይ ሊያሠልፏቸው ይችላሉ? እንደገና፤ ይህ ነው ከዚህ ወዴት? በማለት በዚህ ጽሑፍ ለመግለፅ የፈለግሁት። እናም ወደ ሶስቱ የጠሩ ጉዳዮች እንመለስ።

### አንደኛ የጠራ የትግል ዓላማ መኖር ነው፤

ይህ እንግዲህ በግልፅ የሠፈረ ራዕይ ተነድፎ፤ በተራ ቅደም ተከተል የተቀመጠ የትግል መመሪያ ነው። ባሁኑ ሰዓት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት አንፃር፤ ሁላችንም የሚያስማሙን መሠረታዊ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፤

**፩ኛ፤ ኢትዮጵያ፤ በኢትዮጵያዊነታችን የምንኖርባት ሀገራችን ናት። ኢትዮጵያዊያን አንድ ነን፣ የኢትዮጵያ ሀገራችን ዳር ደንበር መከበርና መጠበቅ አለበት።**

**፪ኛ፤ ኢትዮጵያዊያን፤ ሁላችንም እኩል ኢትዮጵያዊያን ነን፤ የያንዳንዳችን ኢትዮጵያዊያን የግለሰብ ዴሞክራሲያዊ መብታችን እኩል መከበር አለበት።**

**፫ኛ፤ በኢትዮጵያ ሀገራችን የሕግ የበላይነት ይከበር፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሰፈነባት ኢትዮጵያ ትመሥረት። እያንዳንዳችን በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ሠርተን ሀብት አፍርተን የምንኖርባት ሀገራችን ትሁን።**

**፬ኛ፤ አምባገነኑና አድሎኛው የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት ተወግዶ፤ የኢትዮጵያዊያን መንግሥት፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ፍቃድና ፍላጎት ይቋቋም።**

ከነዚህ መሠረታዊ ዕሴቶቻችን የተገነባ ራዕይ መነደፍ አለበት። ይኼን ይዘን ወደፊት መሄድ እንችላለን።

**ሁለተኛው አንድ የጠራ ድርጅት መመሥረት ነው፤**

በቁጥር አንድ የተቀመጠውን የትግል ራዕይ ይዞ፤ ከዚህ ራዕይ የሚፈልቁትን የትግል ሂደቶች በቅደም ተከተል ለማካሄድ፤ ከሞላ ጎደል አብዛኛውን ኢትዮጵያዊያንን ወደ አንድ የማሰባሰቡና የማዋቀሩ ጉዳይ ነው። ከዚህ ላይ መታወቅ ያለበት፤ ከላይ በቁጥር አንድ የተዘረዘሩትን ሀገራዊ መታገያ ዕሴቶች ተንተርሶ የሚነደፍ ራዕይ፤ የሚጠይቀው ነገር ቢኖር፤ ኢትዮጵያዊነትንና ለኢትዮጵያዊነት መቆርቆርን ብቻ ነው። የየግል መቧደኛ ድርጅትን አይጠይቅም። እናም አስፈላጊ አይደለም ማለት ነው። ታዲያ የሚያስፈልገው አንድ ድርጅት ብቻ ነው። ይህ ድርጅት ደግሞ ተልዕኮው ራዕዩን ገሃድ ማድረግ ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ ያለ የሌለ ጉልበትና ሀብታችንን ባንድ ማቅረብና ማጠቃለል የያንዳንዳችን ግዴታ ነው። ወደዚህ ድርጅት እያንዳንዳችን የምንመጣው በግለሰብ እንጂ በድርጅት መሆን የለበትም። ለሀገር ጉዳይ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እኩል ኃላፊነት አለበት፤ ተደራጀም አልተደራጀም።

**ሶስተኛው ብቃትና ጥራት ያለው አመራር ማዘጋጀት ነው።**

በቁጥር አንድ የተቀመጠውን የትግል ራዕይ ይዞና በቁጥር ሁለት የተዋቀረውን ድርጅት መሥርቶ፤ ይህን ሀገራዊ ተልዕኮ፤ አንድ ትግል፣ አንድ ግብና አንድ አጀንዳ፤ በብቃትና በጥራት የሚያከናውን አመራር የማዘጋጀቱ ጉዳይ ነው። ሀገራዊ ራዕዩና የትግል ድርጅቱ ብቃት ያለው አመራርን ግድ ይላል። በቀላል የሚታይ ጉዳይ አይደለም። ከፍተኛ ጥንቃቄን ይጠይቃል። የአብዛኛውን ስምምነት ይጠይቃል። የግልን ወይንም የቡድንን ፍላጎት ሳይሆን፤ የሀገርን ጉዳይ ቅድሚያ መስጠትን ግድ ይላል። በሚሠፍረው ሕግና ደንብ መገዛትን ግድ ይላል። ለብዙኀኑ ፍላጎት መገዛትን ግድ ይላል። ይህ ታሪካዊ ኃላፊነት ነው። ይህ ትውልዳዊ ኃላፊነት ነው። ይህ ሀገራዊ ኃላፊነት ነው። ከመካከላችን ለዚህ ብቁ የሆኑ አሉ። ከሌላ ቦታ አይበቅሉም። ከፍተኛ ጥንቃቄ ሠጥተን ይሄን ካደረግን፤ አስተማማኝ የሆነ ድል ብቻ ሳይሆን፤ አስተማማኝ የሆነ የወደፊት ይኖረናል።

**ከሌሎች የምንማረው፤**

ለግለሰብ ወይንም ለቡድን ሀገራችንን መያዣ አናደርግም። ለቡድኑ ሥልጣን ብልግና፤ ወጣቱ ሕይወቱን አይሠጥም። በአንድነት ሁላችን መቆም አለብን። እስኪ ከሶሪያና አሁን በዚህ ሰዓት ከሚካሄደው ከግብፅ የምንማረውን እናጢን፤

<u>**ከሶሪያ፤**</u> በትንሽ የሀገሪቱ አንድ ክፍል ተመሥርቶ ባንድ አካባቢ ተመርኩዞ፤ የአስተዳደር መረቡን የዘረጋ ገዢ ቡድን፤ ዋና መሣሪያው የሕዝብ ድጋፍ ሳይሆን፤ ጉልበቱና አረመኔነቱ ናቸው። ሰላም በሀገር ሊሠምር የሚችለው፤ ይህ ቡድን ሲወገድ ብቻ ነው። ይህ ቡድን ለአረመኔነቱ ለከት የለውም። ኑሮ እያሽቆለቆለ መሄድ ብቻ ነው ያለው ግዴታ። ሕዝቡ በኅብረት መነሣት አለበት። የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር ከአሰድ ጋር አንድ ነው።

<u>**ከግብፅ፤**</u> ሕገ መንግሥቱን ለቡድን ጥቅም ማራመጃ ሲያደርጉት፤ ሕገ መንግሥቱ ከሀገር ሕልውና በፊት አለመምጣቱን ነው። ተመረጥኩ ብሎ ሥልጣኑን እንደልቡ ለቡድን ጥቅም ማካበቻ ሲያደርጉ፤ ከሕዝቡ ፍላጎት ውጭ ሆኗል ማለት ነው። የሕዝብ ፍላጎት ከሀገር ሕልውና ጋር የተያያዘ ነው። የኛ ሕዝብ ይኼን ገሃድ ለማድረግ፤ በምልዓት መውጣት አለበት። በግብፅ በሕዝብ ብልጫ ተመርጫለሁ ብሎ ያሻውን ለማድረግ የተነሳው የሞርሲ ቡድን፤ በሕዝቡ ተተፍቶ ይኼው በቁጥጥር ሥር ውሏል። የሚቀጥለውን መተንበይ ባይቻልም፤ የግብፅ ሕዝብ ዓይኖቹን እንደማያዞር መናገር ይቻላል። በሃሰት በኢትዮጵያ ሕዝብ በ99.6% ተመርጫለሁ የሚለው የትግሬዎች ነፃ አውጪ ቡድን፤ ሕገ መንግሥቱን የግሉ መ፣ ኣሪያው፣ መንግሥታዊ መዋቅሩን የድርጅቱ አሽከር፣ የሀገሪቱን ንብረት የማጀቱ ዕቃ በማድረግ፤ ከዕለት ወደ ዕለት የከፋ ኑሮ ለኢትዮጵያዊያን ዕጣ ሠጥቷል።

ሌላ ምርጫ የለንም። ግዴታችን ይህና ይህ ብቻ ነው። በእርግጥ አሁን ባለንበት የፖለቲካ ምኅዳር፤ ጦርነት ይብቃ፤ በጦርነት ምንም ትክክለኛ መፍትሔ አይመጣም፣ በሰላም መፍትሔ የሚገኝበትን መንገድ መፈለግ አለብን፣ ገዢውን ቡድን

ወደ ውይይት ማቅረብ ይቻላል፣ . . . የሚሉ እንዳሉ ግልፅ ነው። ለኔ ይኼ ታሪክ የማይመሰክርለት በምኞት ላይ የተመሠረተ ግንዛቤ ነው። የዚህ ግንዛቤ ታላቅ ክስረቱ፤ በአምባገነኖች ላይ እምነት መጣሉ ነው። ትኩረቱ በገዢዎች ርህራሄ ላይ የተተከለ ነው። ለኛ ግን ትኩረታችን የሕዝቡ እዮታና የታጋዩ ክፍል መሆን አለበት። ትኩረቱ የሕዝቡ ሥቃይ መቼ ነው የሚያበቃውና ይኼን ተግባራዊ ለማድረግ የሚተካው መንግሥት ምን ይሆናል፣ እንዴት ይመሠረታል፣ መቼ ይመሠረታልና የመሣሠሉት መሆን አለባቸው። ይዘቱ፣ ቅርፁና አጥንቱ ያስጨንቀን። ስለ አምባገነኑ መጨነቅ የኛ ተልዕኮ አይደለም። ያ የሱ የቤት ሥራ ነው። ማወቅ ያለብን ደግሞ፤ ከኛ የበለጠ፤ መሠሪ ስሌቱን ራሱም ሆነ የሚዶልቱለት ስላለው ለእሱው እንተውለት።

ገዢዎችን በመለመን ሥልጣናቸውን ያጋራሉ የሚለውን ሰበካ ታሪክ አይመሰክርለትም። በዓይኖቻችን የሶሪያውን አሳድ እያየነው ነው። ሙባረክም የተጓዘው፣ ጋዳፊም የተጓዘው፣ መንግሥቱ ኃይለማርያምም የፈረጠጠው በአንድ መንገድ ነው። መንገዱም ሂትለር የሄደበት፣ ሞሶሎኒ የሄደበት፣ ቻውሲስኮ የሄደበት፣ ባቲስታ የሄደበት፣ . . . ብዙ መቁጠር ይቻላል። ታሪክ ይሄንን ነው የዘገበው። የኛዎቹን አምባገነኖች የተለዩ አድርጎ መመልከት የተሳሳተ ሲከፋም አስሊና አዘናጊ ተግባር ነው።

የድርጅቶች የመጀመሪያ ተግባር፤

በአሁኑ ሰዓት ያሉት ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ለአባሎቻቸው ትክክለኛውን ሀገራዊ የፖለቲካ እውነታ ማስተማር አለባቸው። ትክክለኛው የሀገራችን የፖለቲካ እውነታ ደግሞ፤ የሕልውና ትግል በማድረግ ላይ መሆናቸውን፣ የዴሞክራሲ ጥያቄ ወቅቱ የዚህ ተከታይ እንደሆነ፤ በውስጥ አሠራራቸው ደግሞ ዴሞክራሲያዊ አሠራርን የተከተለ መሆን ያለበት መሆኑ ነው። ከዚህ ላይ አንዳንዶቹን ድርጅቶች ከሌሎች አጥብቆ የሚለያቸው ነጥብ አለ። ይኼን አድበስብሶ ማለፍ አይቻልም። ለምሳሌ "ኦሮሞነቴን አስቀድሞ ያልተቀበለ ኢትዮጵያዊነት ገደል ይግባ!" የሚለውን አባባል እንውሰድ። ምን ማለት ነው። ምንጩ ከየት እንደሆነ ከሥር አሳያለሁ፤ ለአሁኑ ግን ምን ማለት ነው በሚለው ላተኩር። የማይገናኙ ነገሮችን ባንድ አለመጓዛቸውን የቀድሞዎቻችን ሲያመላክቱን፤ "ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ!" ይሉ ነበር። "ኦሮሞነቴን አስቀድሞ ያልተቀበለ ኢትዮጵያዊነት ባፍንጫዬ ይውጣ!" ለሚሉት የሚሠጥ መልስ ነው። በጣም የሚገርመው፤ ይኼን የሚሰብኩት ሰዎች፤ በውጭ ሀገር፤ ጥገኝነትን ጠይቀው፣ መቀበል ብቻ ሳይሆን፤ ዜግነትን ጠይቀው ተቀብለው ኑሯቸውን የሚመሩ መሆናቸው ነው።

አንድ ሴት ወይንም ወንድ ኢትዮጵያዊ ለመሆን፤ የትውልድ ሀረጉ የግድ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ አማራ፣ ደቡብ፣ አፋር፣ ሶማሌ፣ አኙዋክ ወይንም ቤንሻንጉል መሆን ግዴታ አይደለም። እስካሁን ድረስ፤ ኢትዮጵያዊነት፤ ከኢትዮጵያዊ ወላጆች መገኘት ወይንም ለኢትዮጵያዊነት ባለው ተቆርቋሪነት የተሠጠ ሀገራዊ ዜግነት ነው። በእርግጥ የመጣ የሄደው መንግሥታዊ መዋቅሩን የጨበጠው ሁሉ እንዳሻው ሲጠመዝዘው መኖሩ የታወቀ ነው። ሆኖም ግን ኢትዮጵያዊነት፤ ለወደፊቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ በሚረቀቀውና በሚፀድቀው ሕገ ደንብ መሠረት፤ ትክክለኛ ሕጋዊ ትርጉሙ፤ ለሁላችንም የሚሠራ፤ በግለሰቡና በቀሪው ኢትዮጵያዊያን መካከል የሚኖረውን ኅብረተሰባዊ ግንኙነት የሚገልፅ ሀገራዊ ዕሴት ነው። በምሳሌ ለመጠቆም ያህል፤ ለአንድ ልጅ የወላጆቹ ኢትዮጵያዊ መሆን በቀጥታ ኢትዮጵያዊነትን ያስገኝለታል፤ በተጨማሪም በምናልባት ደረጃ፤ የኢትዮጵያዊያንን ጥቅም የኔ ብሎ ለቆመና በተግባር ላሳዬም ኢትዮጵያዊነት ሊለገስ ይችላል።

እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን፤ ኢትዮጵያዊነት፤ አንድን ግለሰብ ከቀሪዎቹ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ጋር የሚያዛምድ መሆኑን ነው። ኢትዮጵያ ሀገር ናት። ኢትዮጵያዊነት የዚች ሀገር ዜጋ መሆን ነው። እናም ኢትዮጵያዊነት የግለሰብ ጉዳይ እንጂ፤ ወገናዊ የሆነ የቡድን ዕሴት አይደለም። ስለዚህ እኔ ኢትዮጵያዊነቴ፤ አባቴ አማራ እናቴ ኦሮሞ ስለሆነች አይደለም። ከአንድ አካባቢ የግድ ወላጆቼ መምጣት የለባቸውም። ከተለያዩ አካባቢዎች ወይንም ደግሞ ከአራትና አምስት የኢትዮጵያ ክፍሎች የተገኙ ሊሆኑ ይችላሉ። በምንም መንገድ ቢሆን፤ አንዱን ብቻ ወራሽ ልሆን አልገደድም። ከነዚህ መርጬ ባንዱ በኩል ኢትዮጵያዊ የመሆን አባዜ፤ መያዣ የሌለው ደንባራ ቀመር ነው። ብዙ ከኤርትራዊያን የተወለዱ ግለሰቦች፤ ኢትዮጵያዊ ነን በማለት በኢትዮጵያ የሚኖሩ እንዳሉ የማናውቅ የለንም። ከጃማይካ ኢትዮጵያዊ ነን ብለው ፈልሰው የመጡ እንዳሉ ብዙዎቻችን እናውቃለን። የእንግሊዝ፣ የካናዳ ወይንም የአሜሪካን ተወላጅ ሆነው፤ ሀገራችንን በመውደድ፤ በፋሽሽቱ የጣልያን ዘመን ከአርበኞቻችን ጎን በመታገል ወይንም በዓለም ዙሪያ ለነሱ ጥብቅና በመቆም ሆነ ከዚያ ወዲህም በኢሕአፓ አባልነት ሕይወታቸውን የሠጡ እንዳሉ በግሌ አውቃለሁ። እኒህ ግለሰቦች አሁን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት ባስቀመጠው መሥፈርት፤ የኢትዮጵያዊያን ወገኖች የደም ግንኙነት የላቸውም። ታዲያ እኒህ ኢትዮጵያዊነታቸው ከየት ይመነጫል? እንግዲህ አንድ ግለሰብ ኢትዮጵያዊ ነው ሲባል፤ ከዚህ አካባቢ ወይንም ከዚያ አካባቢ መወለዱ የቅድመ ግዴታ ስሌት የለበትም፤ ነገር ግን ከኢትዮጵያዊያን መወለዱና ምናልባትም የኢትዮጵያዊያንን ጥቅም የኔ ብሎ መነሳትን ግድ ይሆናል።

ይኼን መሠረታዊ የሀገር ዜግነት ወደ ጎድን ትቶ፤ ሲዳማነቴን መጀመሪያ ተቀበሉኝና ኢትዮጵያዊ እሆናለሁ የሚለው አባባል ምንጩ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት የፖለቲካ ትግል ፍልስፍና ነው። እዚህ ላይ የፖለቲካ ትግል ያልኩበት ምክንያት አለኝ። የፖለቲካ ፍልስፍና ሊሆን አይችልም፤ መሠረት የለውምና። የፖለቲካ ትግል ፍልስፍና ግን ነው፤ ዒላማ አድርጎ ያነጣጠረበት ግብና ሂደት አለውና። እንዲህ ነው፤ በኢትዮጵያ ያሉት፤ ኢትዮጵያዊያን ሳይሆኑ፤ ትግሬዎች፣

ኦሮሞዎች፣ አማራዎች፣ ሶማሌዎች፣ አፋሮች፣ ቤንሻንጉሎች፣ አደሬዎች፣ ደቡቦች ብቻ ናቸው ብለን ከተነሳን፤ ኢትዮጵያን ለመበታተን ቀላል ይሆንልናል። ብዙ የተከፉ ወገኖች ስላሉ ይህ ስሌት ብዙ ደጋፊዎችን ያስገኝልናል የሚል ነው። ይህ የፖለቲካ ትግል ፍልስፍና ነው። ከላይ እንደጠቆምኩት፤ ኢትዮጵያዊ ነኝ ለማለትም ሆነ ነህ ተብሎ ተቀባይነት ለማግኘት፤ ቅድሚያ ኦሮሞነቴን ወይም ወላይነቴን መቀበል አለባችሁ የሚለው ምንጩ በሀገራችን ያለው የፖለቲካ ትግል ፍልስፍና ነው። ስለዚህ፤ መጀመሪያ የትውልድ ሀረጌን ተቀበሉኝ የሚለው የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር የፖለቲካ ትግል ስሌት ስለሆነ፤ ይኼን ፈላጊዎች፤ ወደፈጣሪው ቡድን፤ ወደ ትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባርና ግቡ ውለው አድረው መወገናቸው አይቀሬ ነው። በቡድን ሙብት መጠለል የሰጎን ራሷን በአሸዋ ውስጥ መቅበር ነው።

ተከትሎ ደግሞ፤ ኢትዮጵያዊነትን የሚፈልጉትና ሌሎች እንዲቀበሉት የሚገፉት አማራዎች ናቸው የሚለው፤ ኢትዮጵያዊነትን ከአማራነት ጋር አንድ ማድረጉ መሠሪ ተንኮል፤ ወንዝ ያማያሻግር ቁንፅል ግንዛቤ ነው። የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር፤ ትግሉን ሀገራችንን በመከፋፈል ሲገፋ፤ በጠላትናት የፈረጀው አማራውን ነው። እናም፤ “የመጥፎ ነገር ሁሉ መነሻውና መድረሻው አማራ ነው። ከዚህ የተነሳ፤ ኢትዮጵያዊነትን የሚያጠብቀው አማራው ነው። ኢትዮጵያዊነትን የሚፈልገው አማራው ነው። አማራነት ኅብረትን ሰባኪ ነው። አማራነት እስካለ ድረስ፤ ኢትዮጵያዊነት አለ ማለት ነው። ስለዚህ አማራውን ማጥቃት አለብን። ሌሎችም እንዲያጠቁት የምችለውን ሁሉ ማድረግ አለብኝ። ከሌሎች አካባቢዎች እንዲፈናቀልና ለብቻው ከሌሎች ጋር እንዳይገናኝ ካደረግነው፤ ኢትዮጵያዊነት እየኮሰመነ ይሄዳል። . . . ” የሚል መሠሪና ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ የአስተዳደር ፍልስፍና በማራመድ ሀገራችንን አደጋ ላይ ጣለ። ይህ ሀገርን ለመበጣጠስ በፋሻስቱ ዘመንና በዘመነ መሳፍንት የተለመደ የትውልድ ቆጠራ ስሌት፤ ከሀገር ጋር ግንኙነት የለውም። ከማንም ይወለድ ወይም ትወለድ፤ ኢትዮጵያዊነት አንድ ግለሰብ ከቀሪዎቹ ጋር ለሚያደርገው ኅብረተሰባዊ ትስስር መመዘኛ ሀገራዊ የዜግነት ደንብ ነው። በፊት በቀረቡት ሶስት ክፍሎች እንዳሳየሁት፤ በሥልጣን ላይ የሚወጡና በሥልጣን ላይ ለመቆዬት የሚጥሩ ግለሰቦችና ቡድኖች፤ ትልቁ መሣሪያቸው፤ ራሳቸውን ሕጋዊና ብቸኛ መሪ ያደርጋሉ። ለዚህ የሚጠቅማቸው ደግሞ፤ እነሱ የሚሠጡት ቃል ትክክለኛ ሌሎች ስህተተኞች አድርገው ነው። እናም የትውልድ ቆጠራው የዚህ ሂደት ክፍል ነው። የፖለቲካ መሣሪያነት። እናም የትውልድ ቆጠራው ጊዜያዊ ነው። በሥልጣን ላይ ያለው ተራዉን እስኪለቅ ድረስ። ኢትዮጵያ ግን ሀገር ናት።

ለኔ የአንድ ኢትዮጵያዊ የትውልድ ቆጠራ ግንዛቤዬ ውስጥ የሚገባው፤ አኙዋክ ስለሆንክ ታረድ፣ አማራ ስለሆንክ ሀብትህ ይዘረፍና ተፈናቀል፤ ተገደል፣ ኦሮሞ ስለሆንክ ተጨፍጨፍ፤ የተባለ ጊዜ ነው። ይኼ ደግሞ ተብሏል፤ ተደርጓል፤ በመፈፀምም ላይ ያለ ነው። ይህ መደረግ የለበትም ብዬ በኢትዮጵያዊነቴ ተነስቻለሁ። ይህን ማድረግ ኢትዮጵያዊ ግዴታዬ ነው። እዚህ ላይ ነው ትውልድ ቆጠራ ለኔ በግንዛቤዬ ዕይታ ውስጥ የሚገባው። ለዚህ ደግሞ ተጠያቂው አሁን በሥልጣን ላይ ያለው አምባገነኑ አድሎኛው የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር ገዢ ቡድን ነው።